# አቅጣጫችን ወዴት ይሆን?

"ቢስሚልላሂር-ረሕማኒር-ረሒም።"

አሥሠላሙ ዐለይኩም ወረህመቱልላሂ ወበረካቱሁ።

ውድ የስልጤ ልማት ማህበር አባላት እንዲሁም ውድ እንግዶች፤

ውድ የጥሪው ተካፋዮች፤

በዛሬው ዕለት በዚህ የስልጤ ልማት ማህበር ባዘጋጀው "ዓመታዊ ጉባኤ እና ባህላዊ ዝግጅት ጥሪ" በመገኘት "አቅጣጫችን ወዴት ይሆን?" በሚል ርዕስ ያዘጋጀኋትን መልዕክቴን ለእናንተ ለማድረስ ዕድል በማግኘቴ ደስታዬ ወደር እንደሌለው ስገልጽላችሁ ከልብ ከመንጨ አክብሮት ነው። በቅድሚያ ግን ይህንን የልማት ማህበር በመመሥረትና  እንዲሁም ማህበሩን በማገልገል ለዛሬው ለ"ዓመታዊ ጉባኤ እና ባህላዊ ዝግጅት ጥሪ" ለጋበዙን ሁሉ ምስጋናዬ ከፍ ያለ መሆኑን ከልብ እየገለጽኩኝ እንኳን ይህን ከፍተኛ መልካም ተግባር ለመሥራት አበቃን እላለሁኝ። አልሐምዱሊልላህ።

እኔ በዛሬው ዕለት እናንተ ከሰማችሁትና ከምታውቁት ውጪ የተለየ መልዕክት ይዤ ቀርባለሁ ብዬ ለመናገር አይደለም። ወይም አሁን በህብረተሰባችን ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ እናንተ ካላችሁ አዲስና የተለየ የመፍትሄ ሐሳብ  ለማቅረብም አይደለም። ነገር ግን ይህ ህብረተሰባችን በተስፋ የሚጠባበቀው ማህበር የወደፊት ዕጣ ፋንታ ምን ይሆን የሚል ስጋት በውስጤ በማደሩ በዚሁ ዙሪያ የበኩሌን ሐሳብና አስተያየት ለማካፈል በመፈለግ ቅንንነት በተሞላበት መንፈስ በመነሳሳት ሲሆን ምናልባት ለሚደረገው ማህበራዊ እንቅስቃሴ እገዛ ይሆን ዘንድ ተስፋ በማድረግም ነው።

ውድ ወንድሞቼና እህቶቼ፤

እስካሁን ከየ አቅጣጫው የተደረጉትና በመደረግላይ ያሉት የህብረተሰባችን እንቅስቃሴዎች ሁላችንንም የሚያበረታቱ ቢሆኑም አሁን ህብረተሰባችን ካለበት ችግር አንጻር ሲታይ  ግን መቼ የነዚህ እንቅስቃሴዎች ውጤት  ተጠቀሚ ይሆናል በማለት ቀኑ እንደራቀብኝ ብገልጽላችሁ ቸኮልክ እንደማትሉኝ ነው። በአገራችን ከሌላው ጊዜ በተሻለ የለውጥ እንቅስቃሴ እየታየ ቢሆንም ከችግሩ ግዝፈትና ጥልቀት አንፃር ሲታይ ግን ግና ጅምር ላይ ነን ቢባል ማጋነን አይሆንም። ሆኖም ህብረተሰባችን ከምንጊዜውም በበለጠ ዛሬ መደሰትና መኩራት ያለበት ይመስለኛል ምንም እንኳን የችግሩ ተጋፋጭ ቢሆንም። ምክንያቱም ከአብራኩ የወጡ ልጆቹ ካለፈው በተሻለ መልኩ ተደራጅተውና ነቅተው፣ ያላቸውን ጉልበትና ገንዘብ መስዋእት በማድረግ አይዞህ ከጎንህ አለን እያሉት ነውና። በያሉበት ሆነው ባቋቋሙት  ድርጅት  በአንድነት ጥላ ሥር ወገናዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ደፋ ቀና እያሉ ነውና። እንደዚህ ዓይነቱ በጎ እንቅስቃሴ ከሁሉም አቅጣጫ መታየት በሁላችንም ዘንድ አንድ ልዩ ስሜት ሳያሳድር አልቀረም። በተለይ ባለፈው በገንዘብ ማሰባሰብ ዝግጅት ላይ በአንድ ምሽት የታየው ከፍተኛ ውጤት ለዚህ እንቅስቃሴ ዋቢ ምስክር መሆኑ እሰየው በርቱ "አሸም" የሚያስብል ነው። አልሐምዱሊልላህ።

እንደምታውቁት ደህና ነገርን ለመስራት መነሳሳትም ሆነ በመስራት ላይ መገኘት እንደሚያስደስት ሁሉ እንቅፋቱም ሆነ ውጣ ውረዱ ያንን ያህል አሰልቺና አድካሚ መሆኑን ከእናንተ የተሰወረ ባይሆንም ደግሜ ላስታውሳችሁ። በመሆኑም በተለይ እኛ ኢትዮጵያዊያን በአገራችን ደረጃ መሠራት ያለባቸው በጣም ብዙ ሥራዎች በመኖራቸው እንደ መጠናቸውም ያህል ብዙ መስዋዕትነት እንደሚጠብቀን በመረዳት ሁላችንም ባለን ዕውቀትና ችሎታ የየበኩላችንን ድርሻ መወጣት እንዳለብን ከሚያስገንዝቡን መንገዶች አንዱ እነሆ አሁን የተሰባሰብንበት መልካም ሥራ በመሆኑ  እንኳን ደስ አለን እላለሁኝ። የአላህ እገዛ አይለየን። አሚን!!

ውድ ወገኖቼ፤

ሁላችንም ባለን ዕውቀትና የማገናዘብ ችሎታ የአገራችንን ህብረተሰብ የአለፈውን የታሪክ ጉዞውንና አሁን ያለበትን የታሪክ ጎዳናውን ለአንድ አፍታ ቆም ብለን በምንቃኝበት ወቅት ሁላችንም የበኩላችንን የተለያዩ ሃሳቦችንና አስተያየቶችን መሰንዘር እንደምንችል በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ከእኔ ሀሳብ ጋር በመስማማትም ሆነ ባለመስማማት ያላችሁ የአመለካከት ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ በጠቅላላው የአገራችንን (ኢትዮጵያ) ህብረተሰብ ስንመለከት ሁሉም እኔ አውቃለሁ፣ እኔ ልናገር፣ እናንተ ዝም በሉ፣ የእኔ ሀሳብና አመለካከት የተሻለ ነው፣ እኔ የምለው ካልሆነ ሌላ ሀሳብ በፍጹም አይሆንም ሲባል ነው የሚሰማው፤ የሚታየው ። መደማመጥ ዬለ፣ መስማማት የለ። እንዲሁም ለተነሳ ሃሳብ (topic) መቋጫ ሳይደረግለት ነው ብዙ ጊዜ ተሰብሳቢዎቹ ሲበታተኑ የሚታየው። እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ አላጋጠማችሁም? ወይም ልትታዘቡ አልቻላችሁም? ለምሳሌ አንድ ሰው ከልቡ ከመነጨ ፍላጎት እንኳን ተነሳስቶ አቅሙ የፈቀደለትን ያህል አንድ በጎ ሥራ በአገር ደረጃ ይሁን በመንደር፣ በትልቅ የህብረተሰብ ስብስብ ውስጥ ይሁን በትንሽ ልንቀሳቀስ ብሎ ለህዝብ ለማስማት አደባባይ ቢወጣ የሚሰጠው ምላሽ በተቃራኒው (negative) ነው። ይህ ደግሞ ምንፈለገ እየተባለ ከጀርባው ሲነገር ነው የሚሰማው። ለአዱኒያ ወይም ለአኼራ የማይሆን ሥራ ፤ ሀሜት አሉባልታ ብቻ። አንዱን በፈለግነው ጊዜና ወቅት ከፍ ከፍ እናደርገዋለን። ያልሠራውን ስራ እንክብለታለን፤ እንጽፍለታለን። ያልሆነውን እንደሆነ አድርገን በውሸት የታሪክ መዝገብ ውስጥ እናስቀምጥለታለን። በተቃራኒው ግለሰቡ የሠራው በጎ ሥራ ቢኖር እንኳ ሥራው ላይጥመን ይችላል። እንንቀዋለን። ለሠራው ስራ ዋጋ ከመክፈል፣ በሃቅ ከመዳኘትና ከማበረታታት አልፎ በተቃራኒው እናጣጥልበታለን። እንዲሁም በውሸት የታሪክ መዝገብ ውስጥ እንመዘግብለታለን። አሁንም ውሸት። ነገም ውሸት። ውሸት። የመደገፍም ሆነ የመቃወም ባህሪያችን ወይም ድርጊታችን ከሌላው ዓለም የተለየ ነው የሚመስለው። የሀሳብ ልዩነቶች መኖራቸውን በመርስታ ወይም ባለማወቅ አይመስለኝም እርስ በርሳችን የመጠፋፋት ያክል ነው የምንደርሰው። የተቋዋሚ አካል ድራሽ እስኪጠፋ ድረስ ነው የምንመኘው። የተቃውሞ ሀሳብ ስለቀረበ ብቻ የመጠፋፋት ደረጃ መዳረሱ ለምን አስፈለገ? መቻቻልና መማማር ለምን ቀረ? ዛሬም ማጥፋት፣ ነገም ማጥፋት፣ ሁሌም ማጥፋት መጨረሻው አጥፍቶ መጥፋት? ሁሉም በየአለበት ይነግሥበታል ሁሉም ይሾምበታል። ከታሪካችን እንደምንረዳው የተሾመለት የነገሠለት አንድም አካል አለመኖሩን ነው የሚሰማው የሚተረከው። ንግሥናም ሆነ ሹመት ከእያንዳንዱ የግል ነፃነት ተጠረቃቅሞ የሚገኝ መሆኑን ኑጉሦቹም ሆነ ሹማምንቶቹ መርሳታቸው ነው የሚያስገርመው። ይህንን ውለታ በፍጹም ረስተው ራሳቸው ወደ ፈለጉት ሥራዓት ይመሩታል። ህብረተሰቡ ራሱ የሚፈልገውን ሥራዓት ፍለጋ ወደ ሌላ አቅጣጫ ያምሳል። የሀሳብና የአቅጣጫ ልዩነት በመኻከል በመፈጠሩ ሌላ ችግር አሁንም ሌላ ጥፋት። ከዓለም ታሪክ እንደምናየው የጥፋቶች ክምችት ስለማያንቀሳቅስ አክስሞ መክሰም፣ አጥፍቶ መጥፋት ይሆናል መጨረሻው። ተጠፍቶም ዕረፍት አይሰጠው። በስሙ እየተለመነ ይድረሰው አይድረሰው አጠያያቂ ቢሆንም የቃላት መዝገብ እየተፈጠረ በአየር ላይ ቤት ይሰራለታል። “ላም አለኝ በሰማይ ወተታንም አላይ” ዓይነት ነገር። ከተለምዶ እንደሚታየው ሁሉም ከባህር ማዶ ዳርቻ ሆኖ መመልከትን ነው የሚመኘው። ከአባቶቻችን የወረስነው የታሪክ ቅርስ ወይስ ምንድን ነው ይህ ደግሞ? በበኩሌ መልስ የለኝም። የህብረተሰባችንማ አዋዋል ዳር ላይ ሆኖ የሚመለከተው መች ጠፋ። በጫካ ውስጥ ያሉ ዝንጀሮዎችም ይመለከቱታል እንደምንም የዘራውን ወይም የተከለውን ለማጥፋት። ጅብም ጨለማን ተገን አድርጎ ይመለከተዋል በረሃብ አለንጋ ተገርፎ የያዛት ምርኩዝ መውደቅ አለመውደቋን። አሞራውም ከሰማይ ወደታች እያንዣበበ ይመለከተዋል ከወደቀበት መነሳት አለመነሳቱን። ያም ሆነ ይህ ሁሉም በጋራ ወይም በተናጠል ከየአቅጣጫው ይመለከቱታል። አቤት! የተመልካች ብዛት። ምስኪን! እጅ አመድ አፋሽ ሲሆን።

ይህ ብቻ አይደለም የኛ ባህሪያት ግትረኝነት፣ ትምክህተኝነት፣ በፍጹም አልሸነፍ አልረታም ባይነት፣ በባዶ መኩራት ትንሽ ሰርቶ ብዙ ማውራት፤ ራስን ያላ ሥራ ከፍ ከፍ ማድረግ፣ ለተፈጠረ ጥፋት ይቅርታ መጠየቅ እንደ ነውር መቁጠር ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉት የእድገት እንቅፋት የሆኑ አመለካከቶችና ድርጊቶች አገራችንን እንደ ወረርሽኝ ነው የወረሩት። ይህንን ለማራጋገጥ ከፈልግን ብዙ ርቀን መሄድ ያለብን አይመስለኝም። በቀላሉ በዙሪያችን የሚገኙትን ትልልቅ ሆኑ ትንንሽ የህብረተሰባችንን ስብስቦች ወይም ቡድኖች ማየቱ በቂ ይመስለኛል። እንዳው በትንሹ ለመታዘብ ያህል ቡና ለመጠጣት የተሰባሰቡ ጋደኛሞች እንኳን በከፈቱት ርዕስ ላይ ሲወያዩ ቆይተው በመጨረሻ ውይይታቸውን በምን መልኩ ነው የሚቋጩት? ለውይይታቸው የመጨረሻውን መቋጫ ሰጥተውት ነው? ብዙ ጊዜ የሚታየው ምንም ዓይነት የመዝግያ ሀሳብ (conclusion) ሳያደርጉለት ነው የሚበተኑት። እንዳውም አንዳንዴ ካለ መደማመጥ የተነሳ መግባባት ሳይፈጠር ቀርቶ ውይይቱ ወደ ግል ጥላቻ ሲሸጋገር ነው የሚስተወለው። እንዳውም መፈነካከት ካልተፈጠረም ጥሩ ነው። አይጣል ከእንደዚህ ዓይነቱ የማይፈወስ ወረርሽኝ። እንደ ምታውቁት ይህ ወረርሽንን በጠቅላላው በአገሪቷ ላይ ስር ሰዶ በመገኘቱ አሁን አገሪቷ ላላችበት የእድገት ደረጃ ካበቋት እንቅፋቶች ውስጥ ቢመደብ የተጋነነ ይመስላቹኋል? ምክንያቱም በአገሪቷ ላይ ከዓመታት ወደ ዓመታት፣ከክፍለ ዘመናት ወደ ክፍለ ዘመናት እየተቀባበለ የሚፈራረቅባትን ድህነት፣ ረሃብ፣ ድርቀት፣ እንዲሁም በሽታ የመሳሰሉ ችግሮችን ቢያንስ ቢያንስ የሚያስታግስና ለተወሰነ ወቅት እንኳን እፎይ የሚያስብል ሥራ ተሰራ ተብሎ ለመናገር ያስደፍራል? ከልመና

የተላቀቅንበት ጊዜ ታውቃላችሁ? እስኪ የምታውቁ ካላችሁ መች እንደሆነ አስሉት። የእድል ጉዳይ ሆኖ ግን በእኔ ዕድሜ አይቼም ሰምቼም አላውቅም። ረሃብ ረሃብ ጦርነት ጦርነት ካልሆነ እንጂ። እንዳውም አንድ መጽሐፍ ሳነብ ይህ ችነፈር የጀመርው በ18ተኛው ክፍለ ዘመን መሆኑን ነው የሚያትተው። ይህ ከሆነ አያሳዝንም! አያስገርምም! እስኪ አስቡት በነዚህ እንደሰንሰለት በተያያዙ የክፍለ ዘመናት ክምችቶች ውስጥ ለዚህ ችነፈር አንድም ዓይነት መፍትሄ ሳይገኝለት መቅረቱ። በዚህ ችግር ዙሪያ አንድም የህብረተሰብ አካል በጋራ ይሁን ወይም በተናጠል አንድም ዓይነት የመፍትሄ ሀሳብ አለማቅረቡ ነው በጣም የሚያስገርመው። አቅርቦም ከሆነ በተግባር ላይ አለማዋሉ ነው በጣም የሚያሳዝነው። እንደዚህ የሰው ህይወት እንደቅጠል በሚረግፍበት አገር ለመቼ እንደተቀመጠ ለማን እንደ ተቀመጠ ነው ለእኔ ሊገባኝ ያልቻለው። ለነገሩማ እንደዚህ ዓይነቱ የመፍትሄ ሀሳብ ቢቀርብ የመተግበሩ ሁኔታ አሳሳቢ ሆኖ ሳለ አገሪቷ ራስዋ ትቀበለው አትቀበለው አጠያያቂ ነው። ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነቱን በጎ ሥራ ዓይታ የምታውቅ አትመስልምና። ታዲያ ለነዚህና ለተመሳሳይ ችግሮች በነዚህ ምዕተ ዓመታት ውስጥ መፍትሄ እንዳይገኝለት ያደረጉት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የተለየ መልስ ሊኖራችሁ ይችል ይሆናል። በእኔ ግምት ግን ከላይ ለመጠቃቀስ የሞከርኳቸው ምክንያቶች ናቸው ብል የጋነንኩት አይመስለኝም። እነዚህ ምክንያቶች አንድነትን የሚያፈራርሱ እንጂ የሚያቀራርቡ አይደሉም። ጥላቻን የሚያጠናክሩ እንጂ ፍቅርን የሚፈጥሩ አይደሉም። ሞራልን የሚያከስሙ እንጂ የሚገነቡ አይደሉም። ምክንያቱም ድርጊቶቹ በእውነት የተገነቡ፣ በሃቅ የተፈረጁ፣ ተገቢውን ሚዛን የተሰጡ አይደሉምና። አብዝተህ ተነዛነዝክ አትበሉኝና የኛ የውይይት ባህል በእንደዚህ ዓይነት ዝብርቅርቅ ባለ ሥነሥርዓት ስለሚካድ ውጤቱ እንደዛው የውሃ ሽታ ሆኖ ነው የሚቀረው። ውጤቱ ዛሬም ውይይት፣ ነገም ውይይት፣ጫጫታ ብቻ፣ ወሬ ብቻ ተግባር የለም ልፋት ብቻ ነው። አንዳንድ ጊዜ የሚደረጉት ውይይቶች እህል ባልተዘራበት ቦታ እህልን ለመሰብሰብ ወደ ማሳ የመሄድ ያክልል ነው የሚቆጠሩት። ከንቱ ልፋት፣ ከንቱ ድካም። ለመሆኑ በእንደዚህ ዓይነት ነው አገር የሚገነባው? በእንደዚህ ዓይነት ነው አገሬን ህብረተሰቤን አገለግላለው የሚባለው? ይህን ነው ለመጪው ትውልድ እንደ ቅርስ የሚተላለፈው? ወይስ "እኔ ከሞትኩ በኋላ ሰርዶ አይብቀል" ነው። ይህ ለእኔ አይገባኝም። ሁላችንም የህብረተሰባችን ጥያቄና ፍላጎት ከተረዳነው፥ እራበኝ ዳቦ ነው እንጂ ያለው ስብሰባ ስብሰባ ብቻ አይደለም። ጠማኝ ውሃ ነው  እንጂ ያለው ውይይት ውይይት ብቻ አይደለም። በጨለማ ውስጥ ነው ያምኖረው አባካችሁ የብርሃኑን መንገድ አፈላልጉልኝ ነው እኮ የሚለን ውድ ወንድሞቼና እህቶቼ። እኛ አዲስ ነገር መፍጠር ካልቻልን ወይም ሰዎች የፈጠሩትና ያዘጋጁትን መገልበጥ (copy) ማድረግ ከተሳነን ከውለታው አንፃር ሲታይ ቢያንስ ቢያንስ ለህብረተሰባችን ከሌሎች እርዳታ የሚያገኝበትና ከቀን ጨለማ የሚላቀቅበትን መንገድ ማፈላለግ ነበረብን። ይህንን ማድረግ ነው የተሳነን ጎበዝ። ይህ የተከሰተው ከላይ እንደጠቃቀስኩት ሆኖ ሳለ  ካለመተባበር፣ ካለመደራጀት፣ በጋር ካለምሥራት፣ የአንድነት ጥቅምን በመርሳት፣ ካለመማማር፣ ካለመቻቻል፣ ወዘተ መሰለኝ በእኔ ግምት።

ውድ የስልጤ ልማት ማህበር አባላት፤

አሁን እኔ ይህንን ሁሉ የማወራው ያለምክንያት ሳይሆን የኛስ አቅጣጫ ወዴት ይሆን? ዛሬ እዚህ የተሰባሰብነው የህብረተሰቡ አካላት ለህብረተሰባችን ያለን አመለካከት ምን ይሆን? ከአብራኩ የወጣንበት ህብረተሰብ የወደፊት እጣ ፋንታው ምን ይሆን የሚለው አሳሰቦኝ እንጂ። እንደ ሰው መሠራት ያለባቸው ሥራዎች በወቅቱ አለመሠራታቸው ነው በጣም የሚያሳዝነውም የሚያሳስበውም። እኛ ከባህር ማዶ ዳርቻ ሆነን በቴሌቭዢን መስኮት እንመልከተው ወይስ መተግበር ያለብንን ግዴታዎች ቀኑ ሳይመሽ ጨለማው ሳይጋርደን በጊዜ እንወጣ ነው ጥያቄው። እርስበርሳችን ተቻችለን፣ አባቶቻችን ያወረሱንን የውይይት ስነሥራዓት አዳብረን፣ በአንድነታችን አምነን ለውጤት እንበቃ ይሆን የሚለው አሁንም አሳሳቢ በመሆኑ እንጂ። አዎ አባቶቻችን አንቱ የሚያስብል የውይይት ሥነሥርዓት ቅርስ አስተላለፈውልናል።  "ባሊቅ፣ አውጫጭኝ፣ ሜልቾ፣ ጎጎት" እና የመሳሰሉትን የስብሰባ ደረጃዎችና ዘዴዎች መቼም የረሳችሁ አይመስለኝም። ስርቆት፣ ጥል፣ ግዲያ እንዲሁም ሌሎች ነገሮች ሲፈጠሩ እንዴት ነበር አባቶቻችን የሚፈቱት? እንዴት ነው ግዲያ የተፈጸመበትን ብጥብጥ የሚያበርዱት? አሁን እኛ እንደምናደርገው ህጋቸውን በጽሑፍ አስቀምጠውት ነው? አይደለም። በጽሁፍ ሳያስቀምጡ በአእምሮአቸው ቀርጸውት አንድ ሳይሳሳቱ ነበር ችግራቸውን የሚፈቱት የነበረው፤ አሁንም ያሉት። መቼም ችግርን መፍታት በፖሊስ ጣቢያም ይቻል ይሆናል። እንደ ምታውቁት ይህ ያአባቶቻችን የችግር መፍቻ ስነሥርዓትም ሆነ ዘዴ ለየት ባለ መንገድ ነው የሚከናወነው። የተጣላን፣ የተገዳደለን በፍጹም በሆነ መልኩ በማስታረቅ እንዳውም ከወዳጅነት አልፎ ጋብቻ እስከ ሚፈጸም ድረስ እንደሚደርስ ለናንተ መናገር አስፈልጊ አይመስለኝም። በአሁኑ ወቅት ይህ ስነሥርዓት የት ሄደ? ረሳነው ማለት ነው? ወይስ አሻሻልነው? እንዳንረሳው እንዴት አስቀመጥነው? የተረከብነውን ቅርስ ማስረከብ ማህበራው ግዴታ ያለብን አይመስልም? ስንቶቻችን ነው በዚህ ዙሪያ ከልጆቻችን ጋር የተወያየንበት? ወይም ከቤተሰቦቻችን ጋር?  እንደ ነገሩማ ቢሆን የአባት ቅርስ ይጠናከራል፣ ይገንባል እንጂ አይፈርስም። ይሰበሰባል እንጂ አይወረወርም። ይሻሻላል እንጂ አይጣልም።

ውድ ወገኖቼ፤

አሁን እኔ ይህ የልማት ማህበር የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ለወረት፣ ለእዩልኝ ሳይሆን ህብረተሰባችን ላለበት ችግር የመፍትሄ ምላሽ ሲመልስ ማየት ነው የምመኘው። ከሌሎች ማህበራት እንደ አየነውና እንደ ሰማነው ዓይነት የዚህ ማህበር ሥራ ልጆች እንደ ሚጫወቱት የሆያ ሆዬ ጨወታ ሳይሆን ከአብራኩ ለወጣበት ህብረተሰብ የአለኝታነት ዋስትና ሲሰጠው ማየትን ነው የምመኘው። የልማት ማህበሩ በመጀመሪያ ደረጃ mission, vision, values, goals and strategies ዓላማው አድርጎ ሲንቀሳቀስ ማየትን ነው የምመኘው። ከዚህ በማስከተል ከሶስት እስከ አምስት አመት የምንመራበት የእስትራቴጂ ዶክመንት ያስፈልጉታል። ድርጅታችን የድርጅት ስርኣት ያሟላ መሆን ይጠበቅበታል። ይህ ካልሆነ ከሸንበቆ የተሰራ ጎጆ ነው የሚሆነው። ማህበሩ ያሉትን አባላቱን አሰባስቦ በተናጠልም ሆነ በጋራ ወገናዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ መንገድ ሲያመቻች ማየትን ነው የምመኘው። ይህ ምኞት በሁላችንም አእምሮ እንደሚጉላላ ነው የምገምተው። የሁላችንም ምኞትና ፍላጎት ይህ ካልሆነ የአንድነታችንና የዓላማችን ስኬት ጥያቄ ውስጥ ነው የሚገባው። ይህ ከሆልነ ደግሞ የእኛ ከዛ ህብረተሰብ መፈጠር ትርጉም ያለው አይመስለኝም። እንደዚህ አይደለም አባቶቻችን፣ እናቶቻችን፣ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ታግለው መንገዱን ያሳዩን። በጨለማ ኖረው ነው  ብርሃን አብርተውልን ያለፉት። የፊደል ቀጠራ ዕድል ሳያገኙ ነው እድል እንድናገኝ ቀንና ለሊት የለፉት። ለነዚህና ለመሳሰሉት ለህብረተሰቡ ችግሮች በአንድነት ሥር በመደራጀት መሥራት ውጤቱ አስደሳች መሆኑን  አስገንዝበውን ነው የተለዩን። በዚህ አጋጣሚ ለህብረተሰባችን ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ እውቀታቸውን እንዲሁም ጊዜያቸውን ሰውተው ያለፍፉትን ሁላችንም እናስታውሳቸው። አላህ የሥራቸውን አጅር በሰፊው ይክፈላቸው። አሚን! እነሆ ሲወጡለት፣ ሲወርዱለት የነበርው የማንነት ትግል ጎኅ ቀዶ እየታየ ነው። ጎኅ ቀደደ "ሶጃት ሶጃን" ብለው በመሰየም ለኛ አስተላልፈውታል። ታዲያ እኛስ?

እንደምታውቁት የህብረተሰባችን ችግር አሁኑኑ ተባብረን አንድ መፍትሄ ካልፈልግንለት እየባሰ እከፋ እየሄደ ነው ያለው። ከአብራኩ የወጡ አካለ ስንኩላን ልጆቹን ወዴት እንደሚወስድ ምን እንደሚያደርግ መላ የጠፋው መሆኑን ሰምታቹሃል? የቲምና የምስኪን ልጆቹስ እጣ ፋንታ ምን ይሆን? በችግር ምክንያት ሌሎች የትምህርት ዕድል ሲያገኙ እነሱ በቀን ጨለማ ተዘፍቀው ዓይን እያላቸው አያዩም፣ ጆኦሮ እያላቸው አይሰሙም፣ አእምሮ እያላቸው አይጠቀሙበትም። የህብረተሰባችን የጤንነቱ ሁኔታ ለእናንተ መናገር አስፈላጊ አይመስለኝም። በውሃ አቅርቦት ችግር ህብረተሰባችን እንዴት እንደሚቸገር ያወቅን ይመስለኛል? ለነዚህና ለማሳሰሉት ችግሮች መፍትሄ አዘጋጅተናል? በእኔ ግምት አዎ አለን ነው የምለው። ይህው አሁን የተሰበሰብንበት ራሱ አንዱ መፍትሄ ነው። አልሐምዱሊልላህ። ግን በመደራጀት ካመንን ብቻ ነው። በአንድነት ሆነን መሥራትን ከተገበርን ብቻ ነው። የውይይት ስነሥርዓችንን አዳብረን ስንወያይ ብቻ ነው። የሀሳብ ልዩነቶች መኖራቸውን ስናውቅ ብቻ ነው። ለተፈጠሩት ቅሬታዎችም ሁኑ ለተፈጠሩት ጥፋቶች በወቅቱ ይቅርታ ስንባባልና ስንቻቻል ብቻ ነው ይህንን የህብረተሰባችን አልፎ ተርፎ ያገራችንን ችግር ለመቅረፍ የምንችለው። ከአላህ እገዛ ጋር አዎ ይቻላል ነው የምለው። እንዳውም ለሌሎች ለአካባቢያቸው ልማት እንደኛው ለሚታገሉ ሁሉ ምሳሌ በመሆን ለብቻዋ ሌላ ክፍለ ዓለም ፈጥራ የምትገኘዋን አገራችንን ከሌሎች ክፍለ ዓለማት ካሉት አገራት ጋር እናቀላቅላታለን  የሚል ምኞት ነው ያለኝ። ማን ያውቃል?! "ኢንሽአላህ"!!

**ዘይኔ ጁሃር ሻፊ**
ኦገስት 22 ቀን 2008
**አሌክሳንድሪ- ቨርጂኒያ**